**ሳምንታዊ ዘገባ (መጋቢት 7 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**ወያኔዎች የጎንደርን ህዝብ የቁም ስቅል እያሳዩ፣ ከጎጃምም ጤፍ ከገበሬው በማስፈራ ራት እየገዙ ወደመቀሌ እያጋዙ ነው፣ መላው ህዝብ አለቅጥ ባሻቀበው የኑሮ ውድነት እየተቀጣ ነው፣ ከ10 እስከ 14 ሚሊዮን የሚደርስ ወገን ከፍተኛ የርሀብ አደጋ አንዣ ቦበታል፣ በባሌ የተቃዋሚ መደበቂያ ይሆናሉ በሚል ፍርሀት፣ በሻኪሶ ደግሞ የአላሙ ዲንን የወርቅ ማምረቻ ክልል ለማስፋት አገዛዙ ደኖችን እያቃጠላቸው ነው፣ ወያኔ አባዱላ በሚል የጡት አሽከሩ ያደረገው ምናሴ ወ/ጊዮርጊስ አማራና ኦሮም በሚል ህ ዝቡን ከፋፍሎ ለማጋጨት በሱልልታ ያደረገው ሙከራ በህዝቡ እምቢታ ከሸፈበት...**

**ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ »»»»»»»»»**

ለዘመናት የኢትዮጵያ ህዝብ ሀብትና ንብረት የሆነውን መተማን ጨምሮ ለም መሬቶችን ከጐንደር ቆርሶ በነዳጅ ለውጦ ለሱዳን የሸጠው መለስ የበሬ ግንባር በምታህል ቦታ ያገኘውን እየቀመሰ እንዳይኖር በግብር እዳና በመዳበሪያ ሂሳብ ናላውን እያናወዙት ከመሆኑም በላይ በፖለቲካ አባልነት እየፈረጁት ቀየውን እየለቀቀ እንዲሰደድ እያደረጉት መሆኑ የሚያሳዝን ደረጃ ላይ መድረሱን በምሬት የጐንደር ህዝብ እየገለፀ ሲሆን አሁን ደግሞ በመለስ ላይ በተቃጣው የግድያ ሙከራ የተነሳ ህዝቡን የቁም ስቅል እያሳዩት መሆኑንም አጋልጠዋል፡፡

በሳለፍነው ሳምንት ደግሞ በጐጃም ውስጥ ጤፍ አምራች ናቸው የተባሉ ወረዳዎች ውስጥ በመዝለቅ ከገበሬው ላይ እያስፈራሩ ጤፍ እየገዙት መሆኑ ታውቋል፡፡

ከጐጃም የደረሰን ዘገባ እንደሚያስረዳው ከሆነ የካቲት 24 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በጐጃም ክፍለ ሀገር ውስጥ በወረዳና ቀበሌ ገበሬ ማህበር ድረስ በመዝለቅ ከገበሬው ላይ ቤት ለቤት እየዞሩ ጤፍ በግዥ እየወሰዱ ሲሆን በአሁን ሰዓት ጐጃም ውስጥ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ድረስ ወርደው የአንድ ኩንታል ጤፍ 550 ብር እንደደረሰና ይህንንም ውጥረት እንዲሰፍን ያደረጉት የወያኔ ወታደሮች መሆናቸው ታውቋል፡፡

የወታደራዊ መኪኖችን ገበሬ ማህበር ድረስ ይዘው ገብተው በግዴታ እንዲሸጥላቸው እያስፈራሩ በ550 ብር ኩንታል እየገዙ በገጠርም ሆነ በከተማ የእህል እጥረት እንዲኖር ሆን ብለው እየሰሩ ያሉ ሲሆን ይህንንም የእህል ግዥ እያካሄዱ ያሉት ለወታደሩ ቀለብ ሊሆን እንደሚችልና ምናልባትም ጦሩ ከዚህ ቀደም የኑሮ ውድነት ዙሪያ ያነሳውን ጥያቄ ለመመለስና ለወታደሮች ቤተሰብ ብቻ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ታስቦ ሊሆን ይችላል ሲሉም ድርጊቱን የተከታተሉ ወገኖች ግምታቸውን ይሰነዝራሉ፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ጐጃም ውስጥ በአሁን ሰዓት የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ ከ550 ብር እስከ 600 ብር የደረሰ ሲሆን በአዲስ አበባ 720 ብር በድሬዳዋ 850 ብር በላይ እያሻቀበ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አስረድቶ በጥቂት ቀናት ውስጥ ይህ ዋጋ ሊቀየር እንደሚችልና እጅግ ሊያሻቅብ እንደሚችል ከየስፍራው የሚደርሱን ዘገባዎች ስጋታቸውን አጋርተውናል።

**በአሁን ሰዓት በአዲስ አበባ ያለው ገበያ**

ጤፍ 720 ብር

ምስር 1 ኪሎ 14 ብር

የሽሮ እህል 1 ኪሎ 12 ብር

ድንች 1 ኪሎ 8 ብር

ነጭ ሽንኩርት 16 ብር

ዘይት 32 ብር ገብቷል።

ከጐጃም ገበሬ በግዴታ በሽያጭ እየተሰበሰበ ያለው ጤፍና ሌሎችም የእህል አይነቶች በመከላከያ መኪና ቮልቮ ባለተሳቢና ሌሎችም መኪኖች እየተጓጓዘ ወደ መቀሌ እንደሚሄድ የአይን እማኞች እየገለፁ ናቸው።

ወያኔ የመሳሪያና የእህል ችግር እንዳያጋጥመን ብለው ባለፈው ዓመት መቀሌ አካባቢ ያሰሩት ትላልቅ መጋዘኖች በመኖሩ አሁንም እህሉ ከጐጃም እየተለቀመ ወደዚሁ መጋዘን እየገባ እንደሆነ ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል።

የወያኔ ባለሥልጣናት የህዝቡን ሀብትና ንብረት በተለያየ መንገድ ሲዘርፉት የቆዩ ቢሆንም አሁንም በአዲስ ስልት ዘረፋ መጀመራቸውን ምንጮች ገለፁ።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የጨው መጋዘን ያላቸው 75 በመቶ ያህሉ ከህወሓት ታጋይነታቸው ወደ ንግድ ውስጥ እንዲገቡ የተደረጉት መሆኑ የታወቀ ሲሆን ሀሙስ ምሽት ጀምሮ ጨው ጠፍቷል በሚል ወሬ አስወርተው የአዲስ አበባ ህዝብ ሲታመስ እንደከረመ ታውቋል።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ የአንድ ኪሎ ጨው ዋጋ ከ0.70 ሳንቲም ተነስቶ 14 ብር ድረስ ሲሸጥ እንደነበረና ይህንንም ቀውስ የፈጠሩት ወያኔና ወያኔዎች ብቻ መሆናቸው ታውቋል።

በተለይም ዛሬ የአንድ ኩንታል ጤፍ 720 ብር፣ የአንድ ኪሎ ሽሮ ከ12 ብር፣ አንድ ኪሎ ምስር ከ16 ብር የሁለት ብር ሳሙና የነበረው 6 ብር ከ50 ሳንቲም መግባቱ ሳያንስ ከመሬት ታፍሶ የሚመጣው ጨው 14 ብር መሸጡ የሚያንገበግብና የወያኔ ሴራ ነው።

ዛሬ ህዝቡ በኑሮ ውድነት ተወጥሮ ባለበት ወቅት በሀገሪቱ ከፍተኛ የረሀብ አደጋ እያንዣበባት መሆኑም ከአለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች ገለፃ ለማወቅ ተችሏል።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እንደነዚህ ድርጅቶች ስጋት ከሆነ ከ10 -14 ሚሊዮን ሕዝብ ለከፍተኛ የረሀብ አደጋ ሊዳረግ ስለሚችል በቂ ዝግጅት ሊኖር ይገባል እያሉ ሲወተውቱ ወያኔ በውድ ዋጋ የጦር መሣሪያ እየገዛ እያከማቸ መገኘቱ አሳፍሪና አሳዛኝ ተግባር ነው ያሉት እነዚሁ የለጋሽ ድርጅት ሠራተኞች በአሁን ወቅት በቦረና በየቀኑ 500 የቀንድ ከብቶች እየሞቱ ነው ሕዝቡ በረሀብ ምክንያት ቀየውን ጥሎ እየተሰደደ ነው:: የወያኔ ባለሥልጣናት ግን ረሀቡ መጠነኛ ነው በቀላሉ እንቆጣጠረዋለን በማለት በህዝቡ ሞት እየተሳለቁበት ነው ሲሉ እያለቀሱ ሲገልፁ ተደምጠዋል::

ዛሬ የሀገሪቱ ህዝቦች ለከፋ ችግር ተጋልጠው በመጪው ጥቂት ቀናት ውስጥ 14 ሚሊዮን ህዝብ ለሀረብ ይጋለጣል ተብሎ ለጋሽ ድርጅቶች እየጮሁና ቅደመ ዝግጅት ለማድረግ እየተሯሯጡ ባለበት በዚህ ወሳኝ ወቅት ከተቃዋሚዎች ጋር ግንኘ -ነት አላችሁ እያሉ ከስራቸው እያባረሯቸው ሲሆን ሕዝቡ በረሀብ ሊያልቅ በዝግጅት ላይ መሆኑም ታውቋል::

በአንፃሩ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በየክልሉ እየዞረ ትርፍ አምራች ገበሬ እያለ ገበሬውን የእራፊ ጨርቅ እየሸለመ ለማታለል ያደረገው ሙከራ ሩቅ ሳይሄድ ገና ከወዲሁ የሚሰራው ሴራ ተጋልጦበታል::

ይህን የመሰለ የከፋ ድርቅ በሀገሪቱ ይከሰታል ተብሎ አለም በተጨነቀበት ወቅት የወያኔ ካድሬዎች ይባስ ብለው በባሌና ሻኪሶ ቦታዎች የሚገኘውን ደን በእሳት ለኩሰው እንዳወደሙት ታወቀ::

በባሌ ዞን ውስጥ አምስት ቦታዎች ለዘመናት በአካባቢ ህዝብ ሲጠበቅ የነበረውን ደን የተቃዋሚ ታጣቂዎች መሸሸጊያ ነው በሚል የወያኔ ባለሥልጣናት ከፍተኛ ስጋት ውስጥ ስለገቡ ብቻ ደኑ እንዲቃጠል ትዕዛዝ ሰጥተው ፍፁም ግንዛቤ የሌላቸው ቡችላ ካድሬዎች ለኩሰውት እየጋየ መሆኑ ታውቋል::

በሻኪሶ ደግሞ ለሼህ አላሙዲን ለ10 ዓመት በኮንትራት የተሰጠ በመሆኑ እና እስከአሁን ሲቆፈርና ሲዛቅ የነበረው የወርቅ ማዕድን በማለቁ በዚያው አካባቢ የሚገኘውን ቦታ አስፍቶ እንዲሰራ ለማድረግ ሲባል መጀመሪያ ደኑ መውደም አለበት ብለው የወያኔ ባለሥልጣናት በማሰባቸው የአካባቢው ህዝብ በማያውቀው ምክንያት ሌሊት ተለኩሶ ለ15 ተከታታይ ቀናት እየተቃጠለና እየወደመ መሆኑን የአይን እማኞች ገልፀዋል::

የወያኔው ተላላኪና ለሆዱ ያደረው የኦህዴድ ሊቀመንበር የኦሮሚያ ፕሬዝዳንት አቶ አባዱላ ገመዳ ወይም ምናሴ ወ/ጊዮርጊስ የአማራንና የኦሮሞን ህዝብ ለማጋጨት ያደረገው ሙከራ በህዝቡ የነቃ ተሳትፎ እንደከሸፈበት ታወቀ::

የካቲት ወር መጨረሻ ላይ በሱሉልታ ከተማ በተዘጋጀው ባዛር ላይ ተገኝቶ ባደረገው ንግግር «የኦሮሚያን ክልል ለማልማት በተለይ የአማራው ህዝብ እየተቀራመተ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ነው ስለዚህ መፍትሄ ሊፈለግለት ይገባል» በሚል በመናገሩ የሱሉልታ ከተማ ነዋሪዎች እጅግ በመበሳጨታቸው የተነሳ ተቃውሞ ለማሰማት ሙከራ ተደርጐ በአካባቢው የእድሜ ባለፀጋዎች ጉዳዩ እንዲቀዘቅዝ መደረጉን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጿል።

በተለይ አንድ በአካባቢው ታዋቂ እና በህዝቡ ዘንድ ትልቅ ክብርና አክብሮት ያላቸው ሰው የአባዱላን ንግግር ካደመጡ በኋላ በሰጡት ምላሽ ላይ «አሁን የተናገርከውን ወሬ አድምጠነዋል። ነገር ግን ይህ ከአንተ አንደበት አይጠበቅም። ይሁንና አሁን በተናገርከው ህዝቡ ምን ያህል እንደተቆጣ የምትመለከተው ነው። እኛ ባንገስፀው ኖሮ ዛሬ የሚፈጠረውን ማየት ይቻል ነበር። ለመሆኑ አማራና ኦሮሞ ከመቼ ወዲህ ነው ተለያይቶ የኖረው?» እንዴትስ በዚህ ዘመን ይህንን የመሰለ ከአንድ መሪ ነኝ ከሚል ካድሬ ሰው ይህን የመሰለ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጭ ንግግር ልታደርግ ቻልክ የሚሉና ሌሎችንም ቁጣ አዘል ምላሽ ሰጥተውታል።

በዚህ ወቅት ሕዝቡ እጅግ በጋለ ሁኔታ ተናጋሪውን በጭብጨባ ያጀቧቸው ሲሆን፣ አባዱላም በእሳቸው ምላሽ በመበሳጨት መሬት በእግሩ ሲደበድብና አምቦ ውሃ አሁንም አሁንም ሲጠጣ እንደነበረ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልጿል።

በበረሀ ተማርኮ ለህወሓቶች የውሃ ጀሪካን እያመላለሰ ለብዙ ዓመታት ያገለገለ መሆኑን በቅርበት የሚያውቁት ወገኖች ገልፀው አሁንም የኦሮሞ ህዝብ እያለው እንዳይኖረው እየተደረገ ያለው በዚሁ ምናሴ ወ/ጊዮርጊስ በተባለው ሰውና መሰል ሰዎች ድልድይነት መሆኑን በርካቶች ይገልፃሉ።

የወያኔ ቀንደኛ አቀንቃኝ የሆነው የሪፖርተሩ ጋዜጣ ባለቤትና ዋና አዘጋጅ አማረ አረጋዊ ሰሞኑን በዱከም በአባዱላ ትዕዛዝ ከ4 ሺህ ካሬ ሜትር በላይ መሬት እንደተሰጠው ከዱከም የደረሰን ዘገባ ገለፀ።

የወያኔ ስርዓት ህዝቡን ረግጦ እንዲገዛ መንገድ እየመራ ያለው ይኸው የቀድሞ የህወሓት ባለሥልጣን አማረ አረጋዊ በቅርቡ ለትምህርት ቤት፣ ለማተሚያ ቤት፣ ለመጋዘንና ለሌሎችም የሚውል በሚል ከ4 ሺህ ካሬ ሜትር በላይ ቦታ የሰጠው ሲሆን ይህንንም የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት የተባለው ምናሴ ወ/ጊዮርጊስ (አባዱላ ገመዳ) እንደሆነ የደረሰን ዘገባ ገልፆ በአሁን ሰዓት እጅግ ለሀገሪቱ ብዙ ሊሰሩ የሚችሉ የኦሮሞ ተወላጅ ባለሀብቶች ጥያቄ ቢያቀርቡም ዱከም የደረቅ ወደብ ስለሆነች መሬት ማግኘት አይታሰብም በሚል እየተመለሱ ለወያኔው ቀንደኛ ሰው ይህንን ያህል መሬት መሰጠቱ የሚያሳዝን መሆኑንም የደረሰን ዘገባ ጨምሮ ገልጿል።

በሳሪስ መንገድ ዮሴፍ አካባቢ በነበረው የሪፖርተር ጋዜጣ ቢሮን በርካሽ ከአዲስ አበባ መስተዳድር የተሰጠው ይኸው አማረ አረጋዊ በዚያ ቦታ ላይ ከ5 ፎቅ በላይ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

የሚሆን እያስገነባ ሲሆን በቅርቡም የማተሚያ ማሽን ከአረብ ሀገር (ዱባይ) ገዝቶ ወደ ሀገር ውስጥ እያስገባ መሆኑን የገለፁት ምንጮች በአሁን ወቅት ደግሞ ዱከም የኦሮሚያ ክልል ሆኖ እያለ እነ አማረ አረጋዊ በሆድ አደሩ አባዱላ ገመዳ ይህን ሁሉ መሬት በነፃ መስጠቱ አለቆቹን ህወሓቶችን ፈርቶ እንደሆነም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በ1997 ዓ.ም በነበረው የምርጫ ሂደት የህገሪቱ ህዝቦች በድምፃቸው ነፃነትን ለመጐናፀፍ ያደረጉትን ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደናቀፈና የወያኔው ዘረኛ ቡድን ኃይሉን በህዝቡ ላይ እያናጠረ እንዲኖር ከፍተኛ ቅስቀሳ በሪፖርተር ጋዜጣ አማካኝነት ሲሰራ የነበረው ይኸው አማረ አረጋዊ መሆኑን የገለፁት ምንጮች ሁለት የጉምሩክ አስተላላፊ ድርጅቶች እንዳሉትም ገልፀዋል::

ወያኔ በአሁን ሰዓት እራሱ በሚሰራቸው ወንጀሎች መልሶ ግራ እየተጋባ መሆኑን በአንክሮ የሚከታተሉ የኢኮኖሚ ጠበብቶች እየገለፁ ይገኛሉ::

ይህንንም ሲያስረዱ በቅርቡ አሮጌና አገልግሎታቸው ያበቃ ብሮችን ብሔራዊ ባንክ መጋዘን ቆልፎባቸው አስቀመጠ ተብሎ አዲስ ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ አሳትሞ ማሰራጨቱ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ ሊቃጠል ነው ተብሎ የተሰበሰበውን ብር መልሶ ገበያ ውስጥ በማሰራጨቱ ከፍተኛ የገንዘብ መዝረክረክ እና የዋጋ ግሽበት እንዲፈጠር ምክንያት ከመሆኑም በላይ የገንዘቡ የመግዛት አቅም እንዲዳከም አርድርጐታል በማለት ገልፀዋል::

ወያኔ እራሱ የፈጠረውንና የሰራውን ወንጀል በሌላ አካል የማላከክ ልምድ ያለው ሲሆን ሰሞኑን ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ በቻይና አሳትሞ ገንዘቡን በሀገር ውስጥ ካሰራጨ በኋላ መልሶ ገንዘቡን አሳትመው ያመጡት ግለሰቦች ናቸው በማለት ከየስፍራው ሀብታም ነጋዴዎችን ለቃቅሞ እያሰረ መሆኑም ታውቋል::

በርካታ ነጋዴዎች ማዕከላዊ እስር ቤት ከመታሰራቸው በተጨማሪ እስከ ዛሬ ሲሰሩበት የነበረውን ብር እንዳያንቀሳቅሱ ለባንክ ትዕዛዝ መስጠቱንም ለእስረኛ ቤተሰቦች ቅርበት ያላቸው ወገኖች ይገልፃሉ::

ሀሙስ እለትም በተመሳሳይ ጥቁር ገበያ ተብሎ የሚታቀው የውጭ ገንዘብ መንዛሪ ግለሰቦች እስከዛሬ በተዘዋዋሪ ሕጋዊ የሆነ ግብር እንዲከፍሉ ተደርጐ ዛሬ ወያኔ እራሱ በፈጠረው ወንጀል ምክንያት የተነሳ ሱቆቻቸው ከመታሸጉም በላይ በሱቆቻቸው ውስጥ የነበሩ የሀገር ውስጥና የውጭ ገንዘቦች በደህንነት እንዲዘረፍ ማድረጉንም በስፍራው ሁኔታውን የተከታተሉ የአይን እማኞች ገልፀዋል:: እነዚህ ጥቁር ገበያ የምንዛሬ ሥራ የሚሰሩት ነጋዴዎች ሱቆቻቸው እስከታሸገበት ሀሙስ መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም ምሽት ድረስ 1 ዶላር 12 ብር እየመነዘሩ እንደነበረም ለማወቅ ተችሏል::



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በአሁን ወቅት በሀገሪቱ ታትሞ የተሰራጨው ብር በመብዛቱ የተነሳ ብሩ የመግዛት አቅም ተዳክሞ ቅጠል የመሸከም ያህል መድረሱንም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በምሬት እየገለፁ ይገኛሉ፡፡



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com